የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ህዳር ፲፱ ቀን ፪ሺ ህ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 1
ADDIS ABABA November 29, 2007


ማውጫ


የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .. ገጽ ፫ሺህ፱፻፶


CONTENTS


Ethiopian Railway Corporation Establishment Council of Ministers Regulation ......................... Page 3950


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፩/፪ሺ ህ

## የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፩/፪ሺ ህ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

፪. መቋቋም

፩. የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ ‹‹ኮርፖሬሽን›› እየተባለ የሚጠራው) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡

፪. ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

## Council of Ministers Regulation No. 141 /2007

## ETHIOPIAN RAILWAY CORPORATION ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Ethiopian Railway Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 141/2007

2. *Establishment*

   1) The Ethiopian Railway Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.
   2) The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩/ የባቡር ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን መገንባት፤

፪/ የጭነት የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማካሄድ፤

፫/ የመንገደኞች የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማካሄድ፤

፬/ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

፮. ካፒታል

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፫ ቢሊዮን (ሦስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯፻፶ ሚሊዮን ብር (ሰባት መቶ ሃምሣ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ሊጠየቅ አይችልም፡፡

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፲፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Supervising Authority*

The Ministry of Transport and Communications shall be the supervising authority of the Corporation.

4. *Head Office*

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Corporation is established are:

1) to build railway infrastructure;
2) to operate cargo railway transport services;
3) to operate passenger railway transport services;
4) to engage in other related activities necessary for the attainment of its purpose.

6. *Capital*

The authorized capital of the Corporation shall be Birr 3,000,000,000 (Three Billion Birr) of which Birr 750,000,000 (Seven Hundred Fifty Million Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Corporation is established for an indefinite period of time.

9. *Effective Date*

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 29 day of November, 2007

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE
FEDERAL DEMOCRATIC EREPUBLIC OF
ETHIOPIA